የአፋር ህዝብ ፓርቲ Afar People's Party

# ከአፋር ህዝብ ፓርቲ ወቅታዊ ሁኔታዎችን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ

የአፋር ህዝብ ፓርቲ ወደ አገር ቤት በመመለስ እንደገና ተደራጅቶ በይፋ ስራ ከጀመረ 7 ወራት ገደማ አስቆጥሯል። ፓርቲያችን በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥም የተለያዩ አገር አቀፋዊ የፖለቲካ መድረኮች ላይ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ አገራችን ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለምታደርገው ሽግግር የበኩሉን አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል። በሌላ በኩልም ፓርቲያችን በክልሉ ፖለቲካ መሪ ተዋናይ ከሆኑ የፖለቲካ ሃይሎች እና አገራዊ ለውጡ ወደ ክልላችን እንዲመጣ ሲታገሉ ከነበሩ የለውጥ ሃይሎች ጋር በጋራ በመስራት ክልሉ አገር አቀፉን ለውጥ እንዲቀላቀል የበኩሉን በጎ ተጽዕኖ አድርጓል።

በአሁን ወቅት አገራችን በታሪኳ አይታው የማታውቀውን ለውጥ እያስተናገደች እንደሆነ ከማንም የሚሰውር ሃቅ አያደለም። ይህ የለውጥ ሂደት ጅምሩ እጅግ ተስፋ ሰጪ የነበረ እና አገራችንን ወደ ትክክለኛ የዴሞክራሲ ስርዓት ለማሸጋገር ብቸኛ አመራጭ መሆኑ የብዙሃኑ ኢትዮጵያዊን እምነት ነው። ይሁን እንጂ በአገሪቷ የመጣው ለውጥ ጥቅማችንን አሳጥቶናል ብለው የሚያስቡ ወገኖች ገና በጧቱ ከለውጡ በተቃራኒ በመቆም ለውጡን ለማኮላሸት፣ለማደናቀፍ ብሎም ለመቀልበስ ሌት ተቀን ተግተው እያሰሩ ይገኛሉ።በሌላ በኩልም በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ጥቃቅን እና ወቅታዊ ያልሆኑ አጀንዳዎችን በማጦዝ የለውጡ ግስጋሴ ላይ አሉታዊ ተጽኖ የሚያሳድሩ እና ለውጡን ለሚቃወሙ ፀረ-ዲሞክራሲ ሃይሎች መሳርያ የሚሆኑ ወገኖች እያተበራከቱ መጥተዋል።

የአፋር ህዝብ ፓርቲ /አ.ህ.ፓ/ ይህ በአገራችን ታራክ ልዩ የሆነ የለውጥ እድል እና አጋጣሚ በጥንቃቄ እና በላቀ ብስለት ሊመራ እንደሚገባ በጽኑ ያምናል። ስለሆነም ሁሉም የፖለቲካ ሃይሎች ፀንፍ የረገጠ የፖለቲካ አስተሳሰብን ወደ ጎን በመተው እና ዴሞክራሲያዊ አቋምን በማራመድ የአገራችንን የወደፊት እጣ ፋንታ የመወሰን አቅም ያለውን ይህን ታሪካዊ አጋጣሚ በአግባቡ እና በሰከነ መንገድ መምራት እንደሚገባን አበክሮ ይገልጻል።

የአፋር ህዝብ ፓርቲ የአገራዊ እና ክልላዊ ወቅታዊ ሁኔታዎችን በጥልቀት በመገምገም የሚከተለውን ባለ 6 ነጥብ የአቋም መግለጫ አውጥቷል፣

1. የፖለቲካ መዘውሩን ላለፉት 27 ዓመታት የጨበጠው ገዥው ፓርቲ በክልሉ ሲያደረገው የነበረውን የኒልዮሽ ጉዞ በመግታት የህዝባችንን የፍትህ፣ የዴሞክራሲ፣የእኩል ተጠቃሚነት እና የመልካም አስተዳደር ችግሮች በአገራችን በተጀመረው የለውጥ መርህ መሰረት ጊዜ ሳያሰጥ ሊፈታ ይገባል።

(አ.ህ.ፓ) Ummattah Parti

2. የአ.ህ.ፓ የክልሉ ገዥ ፓርቲ ባለፉት ጥቂት ወራት ውስጥ የደረገው የለውጥ እንቅስቃሴ ብዙ ውስንነቶች የለበት፣ አቃፊ ያልሆነ እና የአገር አቀፍ ለውጡ የሚመራበትን የመደመር እሳቤ የተከተለ አይደለም ብሎ ያምናል። በመሆኑም የክልሉ ገዥ ፓርቲ የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት እና አሳታፊ የለውጥ ሂደትን ለመከተል ያለውን ቁርጠኝነት በተጨባጭ ለማረጋገጥ ግልጽ የሆኑ የፖለቲካ ማሻሻያ እርምጃዎች ሊወስድ ይገባል።
3. የአ.ህ.ፓ አሁን ክልሉን የአጋጠመው የፖለቲካ ችግር በገዢው ፓርቲ ብቻ የሚፈታ አለመሆኑን እና ሁሉም የክልሉ ጉዳይ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ የክልሉ ገዥ ፓርቲ ሁሉንም ወገን ያሳተፈ የሪፎርም እርምጃ ሊወስድ ይገባል።
4. የክልሉ ገዥ ፓርቲ በወረዳዎች እያደረገ ያለው ሪፎርም ህዝቡን ያላሳተፈ ፣ከጠባብ ጎሰኝነት፣ ቡደንተኝነት እና ከሙስና ባልጸዳ መንገድ እያተካሄደ በመሆኑ ለህዝባችን የግጭት መንስኤ እንዳይሆን ሪፎርሙ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ባሳተፈ መንገድ እንዲካሄድ አ.ህ.ፓ ያሳስባል።
5. በአሁኑ ሰዓት በአርብቶ አደሩ ህዝባችን ላይ በተቀናጀ መልኩ ከጎረቤት አገራት ሰርገው በሚገቡ ኮንትሮባንዲስቶች፣ በኢሳ-ሶማሊ እና በዘር ሃረግ በተዛመዱአቸው የቅርብ ደጋፊዎቻቸው እና በጸረ-ለውጥ ሃይሎች የተከፈተውን ጦርነት የፌደራል መንግስቱ ባአስቸኳይ እንዲያስቆም እና ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የሚስችለውን የሁለቱን ክልሎች ወሰን የማካለል ስራ በፍጥነት እንዲያካሄድ አ.ህፓ የፌደራል መንግስቱን አበክሮ ይጠይቃል።
6. በመጨረሻም በክልሉ ሰላም፣ልማት፣ዴሞክራሲ፣ፍትህ እና መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ገዥው ፓርቲ በክልሉ ውስጥ ከሚንቀሳቀሱ ተፎካካሪ ፓርቲዎች፣ምሁራኖች፣የአገር ሽማግሌዎች እና ወጣቶች ጋር በክልሉ ፖለቲካዊ ችግሮች ላይ ለመወያየት የሚያስችል መድረክ እንዲያዘጋጅ እንጠይቃለን።

የአፋር ህዝብ ፓርቲ(አህፓ) Qafar Ummatah Parti